# ለወያኔ ቀዳዳ መስጠት ሀገር ጎጂ ስህተት ነው

ሐተታ ከፍኖተ ሬዲዮ (ግንቦት 2002 ዓ. ም.)

ወያኔ እየተፈረጋገጠ ነው። በዚህም በዚያም ቀውሱ ክሯል። የመለስ ድንፋታ የዚሁ ምልክት ነው። አደብ መግዛት ያቃተው ቸግሮት እንጂ በእንዲሁ በባዶ አይደለም። መሬቴ በሚለው በትግራይም ቢሆን ነገሮች ዘብረቅ ብለውበታል። በተወሰነ ደረጃ ለአረና ተቃዋሚዎች  የተሸነፈ መምሰሉ ምርጫውን ፍትሃዊ ሊያስመስልልኝ ይችላል በሚል በተወሰኑ ቦታዎች ፈቅዶ ለመሸነፍ ተዘጋጅቷል። ምርጫውን በአብዛኛው ማቸነፉ የተረጋገጠ ነውና።

ለምርጫው ወያኔ በበቂ ተዘጋጅቷል። በአፈናውም ደረጃ ሆነ የምርጫ ሳጥኖችን በማዘጋጀቱ ወያኔ እንደ 1997ሉ ሱሬው ወልቆ የሚገኝ አይደለም። ፖሊሶችና ነፍሰ ገዳዮቹን አሰልጥኖና አዘጋጅቶ ይገኛል። የምርጫ ታዛቢዎቹ በአብዛኛው የራሱ ካድሬዎች ናቸው። ዜጎች ያላቸው ምርጫ ወይ በቦታው አለመገኘት ወይም ከተገኙ ባዶ ያልተሞላ ወረቀትን በሳጥኑ መክተት ነው። ከወያኔ የምርቻ ቧልት ፍሬ የሚጠብቁ ተላሎች ቢኖሩም ሞኞችን ማጀብ አንገደድም። ከወያነ ጋር ሰላምና ዕርቅ ሲፈለግ 18 ዓምታት ኣለፉ። ዛሬ ለወያኔ የስላምና ዕርቅ ጉባኤ ጥሪ ማድረግ ሞኝነት ብቻ ሳይሆን ሀገረ አጥፊ ጅልነት ነው። ለወያኔ ቀዳዳ መውጫ መስጠት ማለት ነው። ይህ ደግሞ ከማንም ሀገር ወዳድ የሚጠበቅ ሊሆን አይችልም። ለዚህም ነው ወያኔ ምርጫ የሚለው ላይ በተቻለው መንገድ ማዕቅብ ማድረግ አስፈላጊና ትክክለኛ የሚሆነው።

እየተረገጡ መታገል፤ እየተመተሩ መታገል የሚልን የባርነት ፈሊጥ ሰባኪዎች ዛሬም አሉ። ተጃጅለው የሚያጃጅሉ። ተሸንፈናል እጅ ሰጥተናል በማለት ፈንታ ሌላ ምክንያትን ይደረድራሉ። ከሌሎች ሀገሮች ተመክሮ ስናይ ግን/ ለምሳሌ ሱዳን/ ወያኔ ራሱ በራሱ ሮጦ ቢገኝ ይበልጥ ይጋለጣል። ማሸነፉ ላይቀር መታጀቡ ይበጀዋል እንጂ ኣያሳጣውም። ምርጫው ፍትሃዊ ሊሆን አይችልም ብሎ ከወዲሁ ማጋለጡና አንካፈልም ማለቱ የሚበጅ ና ትክክለኞ የትግል አማራጭ ነበር።  የሱዳን ድርጅቶች እንዳደረጉት። አሊያም በታይላንድና ሌሎች ቦታዎች በታየው መሰረት ሕዝባዊ ተቃውሞንም በአመቺው መንገድ ማደራጀት በተገባ ነበር። ከ 1997ሉ የተማረው መለስ ብቻ ሳይሆን ተቃዋሚውም መሆኑ ቢታይ ጥሩ ነበር። ይህ ግን አልሆነም። ተቃዋሚ የተባሉት መቀናጅት ያቃታቸው ከመሆኑ ሌላ ለወያኔ ከፋፋይ ሴራ አመቺ ሰለባ ሆነው

ቀጥለዋል። በወያኔ ላይ መረባረቡን ትተው እርስ በርስ መናከሱ ላይ አተኩረዋል። ይህም የሕዝብን ትግል ጎጂ ለመሆኑ ጥርጥር የለውም። በወያኔ ምርጫ መንገድ ዛሬ ሆነ ተነገ ወዲያ ስርየት ይገኛል ብለው የሚሰብኩ ተቃዋሚ ሀይሎች ተቃዋሚ ለመሆናቸው ብንጠራጠር ሊፈረድብን አይገባም። ተመክሮን ረግጠው፤ ከ 200 በላይ ንጹህ ዜጋ የወደቀበትን የወደቀለትን ዘንግተው ስህተትን ዳግም ሊፈጽሙ ተነስተዋልናም ነው።

ወያኔ የሚገባኝ ቋንቋ ይህ ነው ብሎ ከነገረን ዓመታት አልፈዋል። ምለላና ማጎንበስ የሚገባው አለመሆኑን በእብሪት ነግሮናል። ከደፈራችሁ ዱር ግቡና ፋኖ ሁኑና ሞክሩኛ ካለ ጊዜ አለፈ። መንገዱን ጨርቅ ያድርግላችሁ ብሎ ቆስቁሶናል። በሆዳችሁ የምገዛችሁ ነኝም ብሎናል በንቀት። ታዲያ ነጋ ጠባ ለወያኔ ሰለባ መሆናችን ምን ይባላል? ተራ ሞኝነት እንዳንልነው ሀገራችንን ሊያጠፋ የሚችል ጉዳይ ነው። በመሆኑም ሁሉም ባሰኘው ይንጎድ ማለቱ በቀላሉ የሚገባን ሊሆን አይችልም። በጋራ ሀገርን ለማዳን መታገል አለብንና ሁሉም በየፊናው፤ ግማሹም ወያኔ በሚፈልገው ጎዳና እየነጎደ የጋራ ትግሉ ሲደፈርስ ማየትን አንፈልግም። ይህ አረመኔ ቡድን ለ19 ዓመታት ሕዝብን ሲያስለቅስ ከመቆየቱ ሌላ ሀገርንም ለኣደጋ ኣጋልጦ ያለ ነው። ኢትዮጵያን ለማዳን ከፈለግን የሀገርን ጠላት ወያኔን ማስወገድ መቻል አለብን ማለት ነው። 19 ዓመታት ወያኔን ለዕርቅና ሰላም በመጥራት ወርቅ ጊዜ ከባከነ በኋላ ዛሬ ካለፈው አልማር ብለን ዳግም ወያኔን ለሰላምና ዕርቅ መጥራቱ አሳዛኝ ይሆናል። ለዚህም ነው ለወያኔ ቀዳዳ አንስጠው ማለቱ ወቅታዊ የሆነው።

ለዘመናት ሰላምን አጥቶ የተሰቃየ ሕዝብ ለቀቅተኛ ሆኖ በጦርነት ጎዳና የሚጓዝ ኣይደለም። ወደዚህ አማራጭ የሚወስደው ወይም የሚያስገድደው ካለ አማራጭ መጥፋቱና ለሰብዕናው ሲል ጦርነትን መምረጡ ነው። ወያኔ በሁለገብ ትግል ተወጥሮ ወደ ሽንፈት ካልተገፋ ሀገርን ማዳን የሚቻል ኣይሆንም። ምለላ አይገባውም--መለማመጥ ሽንፈት ይመስለዋል። ንቀቱ ይጨምራል። ያለፈው አለፈ ብንል እንኳን ዛሬም ወያኔ ንጹህ ዜጎችን እየገደለ ነው። ግፉ ኣላበቃም--ጨመረ እንጂ። ከጊዜ ወደ ጊዜ ወያኔ እየጎመዘዘ መምጣቱ ለሕዝብ ሁሉ ግልጽ የሆነ ጉዳይ ነው። ለዚህም ነው ያለው ብችኛ አማራጭ የመለስን ጸረ ሕዝብ አገዛዝ በጋራ ትግል ጥሎ ሀገርን ማዳን የሚሆነው። የዚህ አገዛዝ ቁንጮዎች የሚሻሻሉ ሳይሆኑ እያደር የሚበላሹ ናችውናም ከእባብ ዕንቁላል ርግብ መጠበቁ የሚጠቅም ሊሆን የሚችል ኣይደለም። የወያኔን ጸረ

ህዝብነት በሚገባ ተረድቶ ይህን ሙኝ ነቅሎ ለመታገል መታገሉ ነው ዋናው ተልዕኮ። የሀገር ወዳድ ድርጅቶችም ዋና ስምሪት መሆን ያለበት በጉንጭ አልፋ ውይይቶች መዳረቅ ሳይሆን፤ በወያኔ የምርጫ ጨዋታ ገብቶ መጫወቻ መሆን ሳይሆን ያ መራራ ግን አይቀሬ በሆነውና መስዋዕትነትን በሚጠይቀው ትግል ተሰማርቶ ለአንዴም ለሁሌም ወያኔን ከነግሳንግሱ ማስወገድ አለብን። ሌላ አማራጭ የለም። አል የሚሉ የተደናገሩ ውይም ይሁነኝ ብለው የሚያደናግሩ ናቸው። የወያኔ መሪዎች ኢትዮጵያን አምርረው ይጠላሉ። የሚጠሏትን ሀገር ሳያጠፉ አያርፉም። ይህን ርኩስ ግባቸውን ያሚሉ ዘንድ ሊተዉ ወይም ዕድል ሊስጡ ክቶም አይገባም። መደናቀፍ አለባችው። ኢትዮጵያን ከማጥፋታቸው በፊት ራሳቸው መጥፋት አለባቸው። አሊያማ አደባባይ ኢየሱስ፤ ቴፒ፤አንዋር መስጊድ፤አረካ፤ወተር፤ጋምቤላ፤አጋዴን፤አዲስ አበባ 1997 ወዘተ ፍጅቶች ሁሌም ህይወት ያልነውን አጀቢ ይሆናሉ። ወሳኝ ትግል የምናካሂደው ለየራሳችንም ስርየት መሆኑ መዘንጋት የለበትም።

ለወያኔ አገዛዝ መፈናፈኛ አንስጠው። ቀዳዳ አንስጠው። መውጫ በር አንጠቁመው። መውጫ መግቢያ አሳጥተን እንጣለው። ክቅርብና ከሩቅ በሀገራችን ላይ ያደቡትን ጠላቶች እናርቃቸው። በቅጥረኞች አንደናገር። የሀገራችንን መረት በያዙት ላይ እንነሳ። ሀገራችንን በትግላችን እናስከብር!